የዘለዓለማዊቷ እመቤታችንን፣ የቅድስት ድንግል ማርያምን እውነተኛ ምንነትና ማንነት በሚመለከት፣ ኹለት፣ ኪዳናውያን፣ የኢትዮጵያ ልጆች፣ በደብዳቤ ያደረጉትን የአስተያየት ልውውጥ፣ በእጦማር ስለተላከልን፥ እኛም፣ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም፣ በዚህ የእውቀት ገበታ ላይ፣ የበኩላችንን፣ ተጨማሪ ማብራሪያ አክለንበት፣ ለብዙዎች፣ የእውቀታቸውን አድማስ እንደሚያሰፋላቸው በማመን፣ በጎዋ አውታር መድረኮቻችን ኹሉ ላይ፣ እንደሚተለው አቀናብረን አቅርበንላችኋል።

ከሀይከን ኃይሌ፡-

እንኳን ለዚህች የተቀደሰች፣ የኅዳር ጽዮን በዓል፣ በሰላም አደረሰን።

መኑ ይእቲ፣ ማርያም ድንግል? ድንግል ማርያም ማናት? ፍጡር ናትን?

ኢትዮጵያዊው ማኅሌታይ፣ ቅዱስ ያሬድ፣ በኅዳር ጽዮን በዓል፣ በዜማ እንዲቀርብ ባዘጋጀው የድጓ ድርሰቱ፡-

**“ማርያምሰ፣ ተሐቱ እምትካት፣ ውስተ ከርሡ ለአዳም፣ ከመ ባሕርይ ፀዐዳ።”**

ማለትም፣

**“ማርያም፣ ከጥንት ጀምሮ፣ በአዳም፣ አካልና ባሕርይ ውስጥ፣ እንደነጭ ዕንቍ ታበራለች።”** በማለት፣

አስከትሎም፡-

**“ዘእንበለ፣ ይትፈጠር ሰማይ ወምድር፥ ወዘእንበለ፣ ይሣረር ምድረ ገነት፣ ሀለወት፣ ስብሕት ቅድስት፥ ወቡርክት፣ ይእቲ ማርያም፣ እንተ ተሰመየት፣ ሰንበተ ክርስቲያን፤ ጽዮን ቅድስት፤ እሞሙ ለሰማዕት ወለእኀቶሙ ለመላእክት።”**

ማለትም፣

**“የሰማዕታት እናታቸው፤ የመላእክት እኅታቸው፤ የተለየች መጠጊያ (ጽዮን ቅድስት)፤ የክርስቲያን ሰንበት (ዕረፍት) ተብላ የተጠራች፣ የተመሰገነች፤ በንጽሕና በድንግልና የተለየችና የተባረከች፣ እርሷ ማርያም፣ ሰማይና ምድር ሳይፈጠር፤ የገነት ምድርም መሠረት ሳይጣል ነበረች!”** በማለት፣ እውነተኛ ምነቷንና ማንነቷን ገሃድ አውጥቶ፣ ማርያም ማናት? ለሚለው ጥያቄ፣ አጥጋቢውን መልስ ሰጥቷል።

**“ሰማይና ምድር ሳይፈጠር፣ እርሷ፣ ማርያም፣ አለች!”** ማለት፣ ምንድር ማለት ይኾን? አዎን! ሰማይን ምድር ሳይፈጠር፣ እርሷ ካለች፣ ፍጡር ናት ልትባል ከቶ የማይቻል መኾኑ ነው፤ ምክንያቱም፣ ፍጡር የምንለው፣ የሰማዩንና የምድሩን ሥነ-ፍጥረት እና የሥነ-ፍጥረት ጓዝ የኾኑትን፣ መላእክትና ሰውን የሚያጠቃልለውን፣ ፍጥረተ ዓለም ነውና።

ከምስጋና፡-

ውድ ሃይከን ኃይሌ፡ እንደምን አለህ? ፈጣሪና በሰውነት የወለደችው እናቱ ማርያም፡ ምስጋና ይድረሳቸው። እኔ ደኅና ነኝ! በዚህ ጽሑፍህ [ምናልባች ቸኩዬና በጥሞና ያላየሁት ካልኾነ በስተቀር፤] እጅጉን ተደንቅያለሁ፤ ጥያቄም አጭሮብኛል።

አምላክን በሰውነት የወለደችው ኢትዮጵያ- ድንግል ማርያም፡ ፍጡር ሰው አይደለችምን? ስለዚህ እኛ የሰው ልጆም ፍጡሮች አይደለንም ማለት ነውን? ፈጣሪ - እግዚአብሔር ቃል- የፍጡሩን ሰውነት፡ ሥጋና ደም እንዲሁም ነፍስን ወስዶ፡ በተዋሕዶ ሰውም ኾኖ የመወለዱና ሰውን የማዳኑ ጉዳይስ እንዴት ሊኾን ነው? እባክህ ያልተረዳሁት ነገር ካለ አብራራልኝ? እግዜር ይስጥልኝ።

ከሀይከን ኃይሌ፡-

የተወደድህና የተከበርህ ምስጋና፤ ያቀረብኸው ጥያቄ፡ ፍጹም ተገቢነትና አግባብነት ያለው መኾኑ፡ የማያጠያይቅ እውነታ ነው፤ ለዚህም መልካም ምግባርህ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ! ለማለት እወድዳለሁ።

የእግዚአብሔር እውነት፡ እውነተኛ፡ መገኛዋና ማደሪያዋ፡ የትና ማን እንደኾነች፣ እንዲሁም፡ የእውነተኝነት ረቂቃዊ ባሕርይዋ፡ ገዝፋ የምትታይበት፡ አካላዊ መገለጫዋ፡ ማን እንደኾነች፡ አስቀድመህ የምታውቀውና የተረዳኸው ምሥጢር መኾኑን አምናለሁ፤ አዎን! ይህች፡ የምታውቃት፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ መገኛዋና ማደሪያዋ፡ የሰው ልጆች፡ የእጅ ሥራ ውጤቶች በኾኑትና "ቅዱሳት" ተብለው በሚጠሩት፡ በብራና እና በወረቀት ላይ በተጻፉ መጽሓፍት ውስጥ ሳይኾን፡ የራሳቸው፡ የሰው ልጆች ሰውነት ውስጥ ባሉት፡ ነፍሳዊ ልቦና እና መንፈሳዊ ኅሊና ነው፥ የዚሁ፡ አካላዊ መገለጫዋም፡ ግዙፉ፡ የሰውነት ሥጋዊ አካል መኾኑ ነው።

አዎን! በዚህ መሠረታዊ እውነተኛ ሓሳብ ከተስማማንና ከተግባባን፡ ላቀረብኸው ጥያቄ፡ እውነተኛውን መልስ ለመስጠት፡ እጅግ ቀላል ኾኖ ይገኛል፤ ይኸውም፡ ይህን፡ የድንግል ማርያምን እግዚአብሔራዊና መለኮታዊ ምንነትና ማንነት ለማወቅና ለመረዳት፡ በመጀመሪያ፡ "'እኔ'፡ የምንለውን፡ የ'እኛን'፡ የእያንዳንዳችንን፡ የ'እኔነት'ና የ'እኛነት' ምነትና ማንነት"፡ በትክለኛ መንፈስ፡ ማወቅና መረዳት ይገባናል። ይህም፡ "እኔ" የምንለውን፡ የግል እኔነታችንን፡ በዚህ፡ በግዙፉና በገሃዳዊው ዓለም ያገኘነው፡ በተባዕትና በእንስት ጾታ፡ ከአባት አብራክ ተከፍለንና ከእናት ማኅፀን ተወልደን የመኾኑ፡ ገሃዳዊ እውነታ ነው።

በመጀመሪያው ሰው፡ በ“አዳም”፡ የኾነውና የተደረገውም፡ ይህው ነው፤ ማለትም፡ “አዳም” ተብሎ፡ ያለወንድና ሴት ጾታ፡ አስቀድሞ የተፈጠረው ሰው፡ ኋላ፡ እናትና አባት ተብለው፡ መሠሎቻቸው የኾኑትን፡ ሴቶችና ወንዶች ልጆችን ለመውለድና ለማስገኘት፡ በወንድና በሴት ጾታ፡ **“ወንድ አዳም”ና “ሴት ሔዋን”** ተብለውና ተለይተው ከመፈጠራቸው በፊት፡ ኹለቱም፡ በአንድ አካልና በአንድ ባሕርይ በተፈጠረው በ“አዳም” ሰውነት ውስጥ፡ በአንድነት ተዋህደው፡ ሕያው ኾነው የመገኘታቸው እውነታ ነው።

ይህንንም እውነታ ማረጋገጥ፡ አስፈላጊ መስሎ ከታየህ በሚል፡ የሚከተለውን ቃል፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ለመጥቀስ ተገድጄአለሁ። ይህም፦

**“ወበዕለት አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም፡ በአምሳለ እግዚአብሔር፤ ገብሮሙ፡ ተባዕተ ወአንስተ። ወሰመየ ስሞ 'አዳም'፡ በዕለት እንተ ባቲ ፈጠሮሙ።”**

ማለትም፡

**“እግዚአብሔር፡ አዳምን፡ በእግዚአብሔር አምሳል በፈጠረው ቀን፤ ወንድና ሴት አደረጋቸው። በፈጠራቸው ቀን፡ 'አዳም' ብሎ ጠራው።”** የሚለው ነው። (ኦሪ. ዘልደት፤ ምዕ. ፭፥ ቍ. ፩-፪።)

አኹን፡ በዚህ፡ መለኮታዊ እውነታ መስተዋትነት፡ የእግዚአብሔርን፡ እውነተኛ፡ የህልውና ሥርዓት ማየትና መመልከት እንችላለን።

ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ አድርጎ፡ በመልኩና በምሳሌው እንደፈጠረው አዳም፡ በመጀመሪያ፡ እንደርሱ፡ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ የኾነው ፈጣሪ፡ ኋላ፡ ሴትና ወንድ አድርጎ በኹለት ጾታ እንደለያቸው፡ ወንዱ አዳምና ሴቷ ሔዋን፡ **“እግዚአብሔር አብ”** ተብሎ፡ <u>በአባትነት</u>፥ **“እግዚአብሔር እም”** ተብላ፡ <u>በእናትነት</u>፡ ከሥነ-ፍጥረቱ ህልውና በፊት፡ በዚህ የመለኮታዊ የመንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸው፡ የመገኘታቸው እውነታ ነው።

በዚህም ህልውናቸውና ማንነታቸው፡ በመንፈስ ቅድሱ ግብር፡ እግዚአብሔር ወልድን በመለኮትነት ወልደውታል። ይህም እውነታ፡ ድንግል ማርያም፡ ፍጡር ሳትኾን፡ ፈጣሪ መኾኗን፡ አስተማምኖ ያስገነዝበናል።

ወላዲተ አምላክ፡ ከሥነ-ፍጥረት አስቀድሞ፡ እግዚአብሔር ወልድን እንዲህ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በመለኮትነት የወለደችው እርሷ፥ ኋላ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ከኢያቄምና ከሓና፡ እንደኛ ሰዎች፡ በፍጡርነቷ፡ ተወልዳ በመገኘት፡ ራሷን፡ ለእግዚአብሔርነት ያበቃችውን፡ የድንግል ማርያምን ሰብአዊት ሰውነት በመዋሓድ፡ እግዚአብሔርን ወልድን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ፡ በሰውነት፡ ለኹለተኛ ጊዜ ወልዳዋለች።

**"ወላዲተ አምላክ"፡ የ"አምላክ እናት" የምንለው፡ ይህ ማንነቷ የሚያመለክተው፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በመለኮትነት በመውለዱ፡ "እግዚአብሔር አብ" እንደምንለው፡ "እግዚአብሔር እም" ማለትም፡ <u>እግዚአሔራዊ እናትነቷን</u> ነው። እንግዲህ፡ ይህ ማንነቷና ምንነቷ የሚያስረዳንና የሚያስገነዝበን፡ ቀድሞ የምናውቀውን፡ የተዋሕዶ ምሥጢር በማጕላት ነው።**

ከምስጋና፦

*ውድ ኪዳናዊ ሃይከን፣ መልእክትህን አንብቤዋለሁ፤ ያላወቅሁት አዲስ ግንዛቤንም አግኝቼበታለሁ። እግዜር ይስጥህ! ነገር ግን፣ ይበልጥ ለመረዳት እንዲረዳኝ፡ "ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ወልድ፡ ከፍጥረት በፊት፣ ከአባቱ ያለእናት፤ ከፍጥረት በኋላ፣ ከእናቱ ከድንግል ማርያም ተወልዷል።" የሚለው ትምህርት፡ አኹን አንተ ከሰጠኸው መልእክት ጋር እንዴት ይዋሃዳል?*

ከሀይከን ኃይሌ፦

እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

*"እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከዓለም መፈጠር በፊት፡ ያለእናት፡ ከእግዚአብሔር አብ ተወለደ፥ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ፡ ከድንግል ማርያም፡ ያለአባት ተወለደ!"* የሚለው፡ የሃይማኖት ትምህርት፡ ከላይ፡ ከቀረበው ሓተታ ጋር፡ በምንም ዓይነት መልኩ፡ የማይታረቅና የማይስማማ ነው፤ አዎን! የእግዚአብሔር እውነት፡ ከሰውና ከሰይጣን ሓሰት ጋር ሊታረቅ የማይችል መኾኑን የምታውቀው ነውና።

ይህ፡ ስሑት ትምህርት፡ ምናልባት ወደሀገራችን ሰርጎ የገባው፡ ከ፩ተኛው ምዕት ዓመት በኋላ ሊኾን እንደሚችል፡ የሃይማኖት መጽሓፍትን በማንበብ፡ ሊደረስበት ይችላል።

በመዝሙረ ዳዊት፡ ምዕራፍ ፪፥ ቍጥር ፯ ላይ፡ **"እግዚአብሔር ይቤለኒ፦ ወልድየ አንተ፣ ወአነ ዮም፡ ወለድኩከ"።**

*ማለትም፡*

**"እግዚአብሔር አለኝ፦ 'አንተ ልጄ ነህ፣ እኔ፡ ዛሬ ወለድሁህ'"።** የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ ማለትም፡ "አንተ ልጄ ነህ" የሚለው፡ እምቅድመ ዓለም፡ አካል ዘእምአካል፣ ባሕርይ ዘእምባሕርይ፡ በመለኮትነት የወለድሁ አንተ፡ ልጄ ነህ ማለት ሲኾን፥ "እኔ፡ ዛሬ ወለድሁህ" የሚለው ደግሞ፡ እምድኅረ ዓለም፡ አካል ዘእምአካል፣ ባሕርይ ዘእምባሕርይ፡ በሰውነት የወለድሁ፡ ያው፡ እኔ ነኝ ማለቱ ነው።

ስለዚህ፡ በኹለቱም፡ የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደታት፡ ወላዲው፡ አንድ መኾኑን አረጋግጦ ያሳየናል።

ስለዚህም፡ *“እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከዓለም መፈጠር በፊት፡ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር እም፡ በመለኮትንት ተወለደ፥ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ፡ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር እም (ከድንግል ማርያም)፡ በሰውነት ተወለደ!”* ማለት ነው።

እኛም፡ በመጀመሪያ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ የነፍስን፡ አካልና ባሕርይ፥ በመካከሉም፡ ከእግዚአብሔር ወልድ፡ የሥጋን፡ አካልና ባሕርይ፥ በመጨረሻም፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ የመንፈስን፡ አካልና ባሕርይ በመንሣት፡ በፍጡርነት ተወለድን፤ ከድንግል ማርያምና ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሥጋ መገኘትና መገለጥ በኋላ ደግሞ፡ በእግዚአብሔር አባትነትና በእግዚአብሔር እናትነት (በቅድስት ሥላሴ)፡ ዳግመኛ፡ በመንፈስ ተወለድን። በኹለቱም ልደታችን የተወለድነው፡ በእግዚአብሔር አባትነትና በእግዚአብሔር እናትነት መኾኑ ነው።

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡-

፩ደኛ፡ በግእዙ፡ "እግዝእትነ!" ለሚለው ቃል፡ "እመቤታችን!" የሚለውን ትር ጉም በመስጠት፡ እስካኹን፡ ለድንግል ማርያም፡ ስንጠቀምበት የቆየነው የመጠሪያ ማዕ ርግ፡ ትክክል አለመኾኑ ነው።

ምክንያቱም፡ የቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ በትክክለኛው የግእዝ ቃል፡ ለ ራሱ ለፈጣሪያችን የሰጠነው፡ የአንድነትና የፈጣሪነት ስሙ፡ "እግዚአብሔር"የሚለውን ሲኾን፡ እርሱን ለብቻው፡ በወንድ ጾታ የምንጠራው፡ በግእዝ፡ "እግዚእነ"፥ በኢትዮጵ ያኛ፡ "አንተ ፈጣሪያችን" ብለን ነው፤ በዚሁ መልክ፡ እርሷን፡ድንግል ማርያምን፡ በግእዝ፡ "እግዝእትነ" ብለን፡ በሴትነትጾታ የምንጠራት፡ ታዲያ ለምንድር ነው? በኢት ዮጵያኛው "አንቺ ፈጣሪያችን" ማለታችን አይደለምን?ይህስ፡ እንደእርሱ ፈጣሪ በመኾ ኗአይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

ግእዙ እኮ፡ ምንጊዜም፡ መሠረቱንና መለኮታዊዉን እውነት አልለቀቀም። የለቀ ቁት የሓሰት ሰዎች ናቸው። ይህን እውነታ የምናረጋግጠው፡ ግእዙ፡ አኹንም፡ "እግዚ እነ"፡ "ጌታችን"ማለት ነው ካልን፡ ታዲያ "ጌታ" ማነው? እግዚአብሔር ብቻ አይደለ ምን? አዎን! ነው እንጂ።

በግእዙ፡ "እመቤት"፥ በኢትዮጵያኛው ደግሞ፡ "የቤት እናት" በሚለው ቃለ ስያሜ፡ ግእዙ፡ በዚህም፡ ያንኑ መሠረቱንና መለኮታዊ እውነቱን አልለቀቀም፤ "እመቤት" የሚለው፡ ለድንግል ማርያም የተሰጠው ያማዕርግስያሜ፡ የእግዚአብሔር ቤት ለኾነችው መንግሥቱና ፍጥረታተዓለማቱ፥ ለእኛም፡ የየግላችንና የቤተሰብ፥

የኅብረተሰብና የአገረሰብ ለኾነውቤታችን፡ እናት የኾነችበትን፡ ሌላውን መለኮታዊ ባሕርይዋን የሚያሳይ ነው።

፪ተኛ፡ አብነታችን በኾነው፡ በግእዙ ቃል መሠረት፡ **"አዳም"** የሚለው፡ የመጀመሪያዎቹ ወንድ እና ሴት፡ የአንድነት ስም፡ በፈጣሪያችው የተሰጣቸው፡ በሦስተኛ ደረጃ ነው፤ ይኸውም፡-

የቅድሚያ ስያሜያቸው፡ "ሰው" መኾኑ፡ **"ወይቤ እግዚአብሔር፡'ንግበር ሰብአ በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ!'"**

ማለትም፡ **"እግዚአብሔርም አለ፤ 'ሰውን፡ በመልካችንና በምሳሌአችን እንፍጠር!'"** በማለቱ ይረጋገጣል፤

ኹለተኛው ስማቸው፡ **"ዕጓለ እመሕያው"** መኾኑ፡ **"ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ እመሕያው፣ በአምሳለ እግዚአብሔር፣ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ።"**

ማለትም፡ **"እግዚአብሔር፡ የሕያዋንን እናት ልጅ፡ በእግዚአብሔር መልክ፡ በወንድነት እና በሴትነት ፈጠራቸው።"** በማለቱ ይረጋገጣል፤

ሦስተኛ ስማቸው፡"አዳም" መኾኑ፡ **"ወእምቅድመ ይትፈጠር አዳም፡ ኢያዝነመ እግዚአብሔር፡ ዲበ ምድር።"** ማለትም፡ **"እግዚአብሔር፡ አዳምን ከመፍጠሩ በፊት፡ በምድር ላይ አላዘነበም።"** በማለቱ ይረጋገጣል።

በመጀመሪያ ተፈጥሮው፡ በግእዙ፡ **"ሰባት ባሕርያት ያሉት"** ለማለት፡ **"ሰብእ"**፥ በኢትዮጵያኛም፡ "ሰው" መባሉ፡ በአንድ በኩል፡ ሦስት ባሕርያት ባሏት፡ በሕያዊት፥ በለባዊትና በነባቢት ነፍስ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ አራት ባሕርያት ባሉት፡ በእሳታዊና በነፋሳዊው፥ በማያዊው (የውኃ)ና በመሬታዊው ሥጋ የተፈጠረ በመኾኑ፡ ገና፡ መንፈስን ሳይጨምር፡ ሰባት ባሕርያት ብቻ ያሉት መኾኑን ያስረዳል።

**"ዕጓለ እመሕያው"** የሚለው ስያሜ ደግሞ፡ ኋላ በፍጻሜው የሕይወት ዘመን፡ ራሱን፡ **"ወልደ ዕጓለ እመሕያው!"** ማለትም፡ **"የሴቷ ሴት ልጅ ወንድ ልጅ የኾንሁት እኔ!"** እያለ ይጠራ የነበረው፡ የእግዚአብሔር ልጅ መሢሕ ኢየሱስ፡ የድንግል ማርያም ልጅ መኾኑን ገልጾ እንደነበረ ኹሉ፡ በፍጥረት መጀመሪያም፡ "አዳም" የተባለው ሰው፡ ኋላ፡በወንድነትና በሴትነት፡ ከኹለት የተከፈሉት፥ ወዲያውም፡ በጋብቻ፡ አንድ የኾኑት፡ የአዳም እና የሔዋንም እናት፡ ይህችው ድንግል ማርያም መኾኗን አረጋግጦ የሚያሳይ በቂ ማስረጃ ነው። (ዘፍ. ፩፥ ፳፮-፳፯፤ ፪፥ ፭።)